# የፖስታ ድምጽ መስጫ መመሪያዎች

<u>እባክዎን የዚህን ወረቀት ሁለቱም ጎኖች ያንብቡ</u>

መርጫለሁ የሚል
ተለጣፊ FPO

1. የፖስታ ድምጽ መስጫ ወረቀት ፓኬትዎ ሁሉም ይዘቶች ያሉዎት መሆኑን ***<u>ያረጋግጡ</u>***።
   የሚከተሉት ነገሮች ሊደርሱዎት ይገባል፦
   - የእርስዎ ድምጽ መስጫ ወረቀት
   - ሚስጥራዊነትን የሚጠብቅ መያዣ
   - ቅድሚያ የተከፈለበት የድምጽ መስጫ ወረቀት መመለሻ ፖስታ
   - “መርጫለሁ” የሚል ተለጣፊ ስቲከር

**ጥያቄ ካለዎት፣ ወዲያውኑ በ1-866-DCVOTES (1-866-328-6837) ያነጋግሩን (1-866-328-6837).**

2. የምርጫ መመሪያውን **<u>በጥንቃቄ</u> ያንብቡ።**

3. ***<u>ለሁሉም ውድድሮች፦</u>***

   - ሰማያዊ ወይም ጥቁር ቀለም ያለው ብዕር በመጠቀም ከምርጫዎ አጠገብ ያለውን ክብ ሙሉ በሙሉ ይሙሉ።
   - በመጻፍ ድምጽ ለመስጠት፣ ክቡን ይሙሉ እና ስሙን በመጻፊያው መስመር ላይ ይጻፉ።
   - ስህተት ከሰሩ፣ ወደ 1-866-DCVOTES (1-866-328-6837) በመደወል አዲስ የድምጽ መስጫ ወረቀት ይጠይቁ።

## <u>ለደረጃ በደረጃ ምርጫ ድምጽ አሰጣጥ (RANKED CHOICE VOTING, RCV) ውድድሮች</u>

ለRCV ውድድሮች፣ በምርጫዎ ቅደም ተከተል መሰረት እስከ አምስት (5) እጩዎችን ደረጃ ሊሰጡ ይችላሉ (1ኛ፣ 2ኛ፣ 3ኛ ወዘተ)። እስከ አምስት እጩዎችን ደረጃ መስጠት ከፍተኛ ደረጃ የሰጧቸውን እጩዎች አይጎዳም።

**አስፈላጊ የRCV የድምጽ መስጫ ወረቀት ደንቦች፦**

ሁሉንም እጩዎች ደረጃ የግድ መስጠት አይጠበቅብዎትም። ለአንድ እጩ ብቻ ድምጽ መስጠት እና ሌሎቹን አምዶች ባዶ መተው ይችላሉ.

- አንድን እጩ ከአንድ ጊዜ በላይ ደረጃ መስጠት የለብዎትም። (በእያንዳንዱ ረድፍ ውስጥ አንድ ክብ ብቻ ይሙሉ።)
- የደረጃ አሰጣጥን መዝለል የለብዎትም። (በተከታታይ ከአንድ በላይ ደረጃ መዝለል በዚያ ውድድር ውስጥ በሁለተኛው መዝለል ቦታ ላይ ድምጽዎ እንዳይቆጠር ያደርገዋል።)
- ከአንድ በላይ እጩዎችን በተመሳሳይ ደረጃ መመደብ የለብዎትም። (በእያንዳንዱ አምድ ውስጥ አንድ ክብ ብቻ ይሙሉ።)

4. የድምጽ መስጫ ወረቀትዎን **<u>በድጋሚ አጣጥፈው</u>** ሚስጥራዊነትን ወደሚጠብቀው መያዣ ውስጥ ያስገቡት።

5. ሚስጥራዊነት የሚጠብቀውን መያዣ ቅድሚያ የተከፈለበት የድምጽ መስጫ ወረቀት መመለሻ ፖስታ ውስጥ **<u>ያስገቡት።</u>** (በድምጽ መስጫ ወረቀት መመለሻ ፖስታ ውስጥ **የእርስዎን** የምርጫ ወረቀት ብቻ ነው ማስገባት የሚቻለው። **የድምጽ መስጫ ወረቀት ከአንድ በላይ ድምጽ መስጫ ወረቀት የያዘ ከሆነ፣ ከድምጽ መስጫ ወረቀቶቹ አንዳቸውም አይቆጠሩም።**)

6. **አስፈላጊ: በድምጽ መስጫ ወረቀት መመለሻ ፖስታ ጀርባ ላይ በመራጩ ቃለ መሃላ ላይ ይፈርሙና ቀን ይጻፉ። የምርጫ ወረቀትዎ እንዲቆጠር የመራጩ ቃለ መሃላውን መፈረም አለብዎት!**

7. የድምጽ መስጫ ወረቀት መመለሻ ፖስታውን **<u>ያሽጉ</u>**።

8. ድምጽ የሰጡበትን የምርጫ ወረቀት ከሚከተሉት መንገዶች በአንዱ ይመልሱ፦

- **በፖስታ**

የድምጽ መስጫ ወረቀትዎን በአካባቢዎ ላለው የፖስታ አገልግሎት ሰጪ ድርጅት ይስጡት ወይም በማንኛውም የዩናይትድ ስቴትስ ፖስታ አገልግሎት (USPS) ፖስታ ሳጥን ወይም በማንኛውም የዩናይትድ ስቴትስ ፖስታ ቤት ያስቀምጡት።

**አስፈላጊ: በፖስታ የሚላኩ የምርጫ ወረቀቶች እስከ ምርጫው ቀን (ማክሰኞ፣ ጁን 16) ፖስታ ቤት መድረስ እንዲሁም ከምርጫው ቀን በኋላ እስከ 10ኛው ቀን ድረስ በምርጫ ቦርድ (BOE) መድረስ አለባቸው። በጊዜ መድረሱን ለማረጋገጥ በተቻለ ፍጥነት ድምጽዎን እንዲሰጡ እና የድምጽ መስጫ ወረቀትዎን በፖስታ እንዲልኩ እንመክራለን.**

- **በማንኛውም 24 ሰዓት ደህንነቱ በተጠበቀ የምርጫ ቦርድ የፖስታ ድምጽ መስጫ ሳጥን (ከአርብ ጀምሮ፣ ከአርብ ሜይ 22 ጀምሮ)**

እርስዎ በDistrict of Columbia ውስጥ በተለያዩ ቦታዎች በሚገኙ 55 የምርጫ ቦርድ የፖስታ የድምጽ መስጫ ወረቀት ማስገቢያ ሳጥኖች ውስጥ የድምጽ መስጫ ወረቀትዎን እስከ ምርጫ ቀን ማክሰኞ፣ ጁን 16፣ 2026 ከምሽቱ 8:00 ሰዓት ድረስ በማንኛውም ጊዜ ማስገባት ይችላሉ።

- **(በቅድሚያ ድምጽ በሚሰጥበት ጊዜ ወይም በምርጫ ቀን ክፍት በሆነ) በማንኛውም የድምፅ መስጫ ማዕከል**

የቅድመ ድምጽ መስጫ ማዕከላት **ከሰኞ ጁን 8 እስከ እሁድ ጁን 14 ድረስ** ከ 8:30 am እስከ 7:00 pm ባለው ጊዜ ውስጥ ክፍት ይሆናሉ፣ እንዲሁም የምርጫ ቀን ድምጽ መስጫ ማዕከላት **ማክሰኞ፣ ጁን 16** ከ 7:00 am እስከ 8:00 pm ባለው ጊዜ ውስጥ ክፍት ይሆናሉ።

የድምፅ መስጫ ወረቀት መመለሻ ፖስታዎን በማንኛውም የድምፅ መስጫ ማዕከል ውስጥ በተጠቀሱት ቀናት እና ሰዓቶች ውስጥ በአካል በመገኘት ድምፅ መስጫ ሰልፎች ላይ ሳይጠብቁ ማስገባት ይችላሉ።

ወደ www.dcboe.org ለሚከተለው ይሁዱ፦

- የBOE ፖስታ ድምጽ መስጫ ወረቀት ማስገቢያ ሳጥን ቦታዎች
- የቅድመ ድምጽ መስጫ ማእከል ቦታዎች
- የምርጫ ቀን የድምፅ መስጫ ማዕከል ቦታዎች
- የድምጽ መስጫ ወረቀት መከታተያ መረጃ
- ስለ ጁን 16፣ 2026 የመጀመሪያ ደረጃ ልዩ ምርጫ አጠቃላይ መረጃ፣ እና
- በተደጋጋሚ የሚጠየቁ ጥያቄዎች (FAQ)
- ስለ ደረጃ በደረጃ ምርጫ ድምጽ አሰጣጥ (Ranked Choice Voting, RCV) መረጃ

### የመምረጥ ተደራሽነት

የአካል ጉዳተኞች እና የእንግሊዝኛ ቋንቋ ችሎታቸው ውስን ለሆኑ መራጮች ተደራሽ የድምፅ መስጫ ማዕከላት፣ ከመንገድ ዳር ድምጽ መስጠት፣ የድምፅ መስጫ ምልክት ማድረጊያ መሳሪያዎች እና ሌሎችንም ጨምሮ ተደራሽ ስለሆኑ የድምፅ መስጫ አማራጮች ለማወቅ ቦርዱን በ 202-727-2194 ያነጋግሩ።

### ጥያቄዎች አሉ?

መልሱን በድረ ገጹ ላይ ማግኘት ካልቻሉ በስልክ ቁጥር 1-866-DCVOTES (1-866-328-6837) ይደውሉልን።

¿Necesita ayuda en su idioma? Llame al 1-866-DCVOTES (1-866-328-6837)

በቋንቋዎት እርዳታ ማግኘት ይሻሉ? በስልክ ቁጥር 1-866-DCVOTES (1-866-328-6837) ይደውሉ።

需要以您的语言帮助？拨打Call 1-866-DCVOTES (1-866-328-6837)

Cần sự trợ giúp ngôn ngữ của bạn? Hãy gọi 1-866-DCVOTES (1-866-328-6837)

Avez-vous besoin d’aide dans votre langue? Appelez le 1-866-DCVOTES (1-866-328-6837)

모국어로 도움이 필요하세요? 1-866-DCVOTES (1-866-328-6837) 로 전화해주세요

DISTRICT OF COLUMBIA
BOARD OF ELECTIONS
WASHINGTON, DC 20003-4733

## በፖስታ ወይም በኦንላይን ለተመዘገቡ ለመጀመሪያ ጊዜ መራጮች አስፈላጊ ማሳሰቢያ

መዝገቦቻችን እንደሚያመለክቱት ከዚህ ቀደም በኮሎምቢያ ዲስትሪክት በፌዴራል ምርጫዎች ላይ ድምጽ አልሰጡም እንዲሁም የመታወቂያ ሰነድዎን (ID) ቅጂ ሳያቀርቡ በመስመር ላይ ወይም በፖስታ ተመዝግበዋል።

በፌዴራል እና በኮሎምቢያ ዲስትሪክት ህግ መሰረት ከሚከተሉት የመታወቂያ ሰነዶች ውስጥ አንዱን ኮፒ ከፖስታ ድምጽ መስጫ ወረቀትዎ ጋር ማቅረብ ይጠበቅብዎታል፦

- የአሁን የሚሰራ በመንግስት t-የተሰጠ ባለፎቶ መታወቂያ፤ **ወይም** የአሁን* የፍጆታ ክፍያ፣ የባንክ ሒሳብ መግለጫ፣ የመንግሥት ቼክ፣ የደመወዝ ቼክ ወይም ስምዎን እና አድራሻዎን የሚያሳይ ሌላ በመንግሥት የተሰጠ ሰነድ።

** የወጣበት፣ የሒሳብ መጠየቂያው ወይም መግለጫው ቀን ከምርጫው ዘጠና (90) ቀናት በፊት መሆን የለበትም። ከጁን 16፣ 2026 የመጀመሪያ ደረጃ ልዩ ምርጫ በፊት 90ኛው ቀን ማርች 18፣ 2026 ነው።*

**የመታወቂያ ሰነድዎን ቅጂ በድምጽ መስጫ ወረቀቱ መመለሻ ፖስታ ውስጥ ያስቀምጡ።**

ከድምጽ መስጫ ወረቀትዎ ጋር የመታወቂያ ሰነድዎን ቅጂ ካላቀረቡ፣ የድምጽ መስጫ ወረቀትዎ እንደ ልዩ (ጊዜያዊ) የድምጽ መስጫ ወረቀት ይቆጠራል፣ እናም የማንነት

መታወቂያዎን ቅጂ እስከ ማክሰኞ፣ ጁን 23፣ 2026፣ 4፡45 pm ድረስ ለምርጫ ቦርድ ካላቀረቡ በስተቀር አይቆጠርም።

ይህንን መስፈርት በተመለከተ ጥያቄ ካለዎት እባክዎ በ 1-866-DCVOTES (866-328-6837) ላይ ያነጋግሩን።

---

**1015 Half St SE Suite, 750 ● www.dcboe.org ● ስልክ (202) 727-2525 ● TTY 711 ● ፋክስ (202) 347-2648**